በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አማላክ አሜን

ብፁእ አባታችን አቡነ ዘርዐ ቡሩክ

በረከታቸዉ ይደርብንና ብፁእ አባታችን አቡነ ዘርዐ ቡሩክ ከአባታቸዉ ከቅዱስ ደመ ክርስቶስ ከናታቸዉ ከቅድስት ማርያም ሞገሳ በ 8 ኛዉ መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ በክብር ተወለዱ ከመወለዳቸዉ አስቀድሞ ቅድመ አያታቸዉ ከኔ ዘር 7ኛ ትዉልድ አንዲት ሴት ትወልዳለች ከርሶም አለምን በጸሎቱ የሚያድን ይወለዳል ብለዉ ትቢት ተናግረዉላቸዉ ነበር። በተወለዱ በ 7 አመታቸዉ ይህን አለም ክፋቱን እንዳላይ አይኖቹን አሳዉርልኝ ብለዉ ጸለዩ አይኖቻቸዉም እስከ 12 አመታቸዉ ማየት አይችሉም ነበር። ከዛም በኋላ የዓለምን ክብር በመናቅ በትምህርት ምክንያት ከሃገር ወደ ሃገር ከገዳም ወደ ገዳም እየተዘዋወሩ ብዙ ታምራትን ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጋር መጋቢት 27 ቀን ዲያቆን ሆነዉ ቀድሰዋል ፤ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሞት ጊዜም ተገኝተዋል በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገድል መጽሃፍ ላይም ሰፍረዉ ይገኛሉ 12 ክንፎችም ተሰተዋቸዋል በግዮን ምንጭ ግሽ አባይ በተባለዉ ቦታ ለ 30 አመታት ጸልየዋል ፤ አሁንም በዛዉ ግሺ አባይ ፈለገ ግዮን ቅዱስ ሚካኤል እና አቡነ ዘርአ ቡሩክ ቤተክርስቲያን በጸበላቸዉ ታምራት እየተደረገ ነዉ ።

ታህሳስ 13 አባታችን አቡነ ዘርዐ ቡሩክን የምናስብበት ቀን ነዉ ከበረከታቸዉ ያካፍለን አሜን

ምንጭ : ገድለ ዘርዐ ቡሩክ እና ተአመረ ዘርዐ ቡሩክ በግዕዝና